# ካላይ ከእጽዋት ጋር ትነጋገራለች

Ursula Nafula
Jesse Pietersen
Mezemir Girma
2
አማርኛ am

ይቺ ካላይ ነች። ዕድሜዋ 7 ዓመት ነው። የስሟ ትርጉም በቋንቋዋ በሉቡኩሱ ‹‹ጥሩዋ ልጅ›› ማለት ነው።

ካላይ ከእንቅልፏ ስትነሣ ከአንድ የብርቱካን ዛፍ ጋር ትነጋገራለች። ‹‹እባክህ አንተ የብርቱካን ዛፍ ትልቅ ሁንና ብዙ የበሳሰሉ ብርቱካኖችን ስጠን›› ትለዋለች።

ካላይ ወደ ትምህርት ቤት ትሄዳለች። በመንገዷም ላይ ከሳሩ ጋር ታወራለች። ‹‹እባክህ ሳር አረንጓዴነትህን ግፋበት እንጂ እንዳትደርቅ።››

ካላይ የዱር አበቦችን አልፋ ሄደች። ‹‹አባካችሁ አበቦች ለጌጥ ጸጉሬ ላይ እንዳረጋችሁ ማበባችሁን ቀጥሉ።››

በትምህርት ቤት ግቢ ካለው ዛፍ ጋርም ካላይ ትነጋገራለች። ‹‹እባክህ አንተ ዛፍ ከጥላው ስር ቁጭ ብለን እንድናነብ ትላልቅ ቅርንጫፎችን አብቅልልን።››

ካላይ በትምህርት ቤቷ ዙሪያ ካለው ቁጥቋጦም ጋር ታወራለች። ‹‹ጠንካራ ሆናችሁ እደጉ፤ መጥፎ ሰዎች እንዳያልፉ አግዷቸው።››

ካላይ ከትምህርት ቤት ወደ ቤቷ ስትመለስ የብርቱካኑን ዛፍ አየችው። ‹‹የብርቱካን ፍሬዎችህ ገና አልበሰሉም?›› ስትል ካላይ ጠየቀችው።

‹‹የብርቱካኑ ፍሬዎች ገና አልበሰሉም›› ካላይ አለች። ‹‹ነገ እመለስና አይሃለሁ የብርቱካን ዛፍ›› አለች ካላይ። ‹‹ምናልባት ያኔ የበሰሉ የብርቱካን ፍሬዎች አዘጋጅተህ ትጠብቀኝ ይሆናል!››

# Global Storybooks

globalstorybooks.net

## ካላይ ከእጽዋት ጋር ትነጋገራለች


Ursula Nafula
Jesse Pietersen
Mezemir Girma


CC BY